# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 09-09-2012 تاريخ Lakk.: No.: 015/stm-abo/2012 رقم

## ከኦነግ ስራ ኣስፈጻሚ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

የኦነግ ስራ ኣስፈፃሚ ኮሚቴ በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግልና በትግሉ ጎራ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ክስተቶች እየተስተዋሉ ባለበት ሁኔታ ከመስከረም 4-9, 2012 ሲያካሄድ የቆየውን ስብሰባ በስኬት ኣጠናቅቆኣል። እየተስተዋሉ የሚገኙት ክስተቶች በኣንድ በኩል ለነፃነት ትግሉ ስኬት የተሻለ እድል የሚያመቻቹ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እንቅፋት የሚደቅኑበት ኣጋጣሚም ይኖራል። በኢትዮጵያ ኢምፓየርና በቀጣናችን በፍጥነት እየተከሰቱ የሚገኙትን ሁኔታዎች የኦነግ ስራ ኣስፈፃሚ ኮሚቴ በስፋት ከገመገማቸው በሁዋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች በማሳለፍ ስብሰባውን ኣጠናቅቆኣል።

የወያኔው ኣምባገነናዊ መሪ የመለስ ዜናዊ ሞት ኣለም ኣቀፉን ማህበረሰብና በተለይም የኢትዮጵያ ህዝቦችን ትኩረት ከመሳቡም ባሻገር ሞቱን ተከትሎ ምን ይከሰት ይሆን የሚል ጥያቄ ጭሯል። ይሁን እንጂ የኣንድ ኣምባገነናዊ ስርኣት መሪ ሞት ለብቻው ለውጥ ያመጣ ይሆናል ብሎ መጠበቅ ስህተት ነው። ስርነቀል ለውጥ ማምጣት የሚችለው የስርኣት ለውጥ ብቻ ይሆናል። ስለሆነም የኢምፓየርነቱ ስርኣት ተለውጦ በሃይል የተያዙት ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው እስከሚወስኑና የዴሞክራሲ፣ የእኩልነትና የነፃነት መብቶች እስከሚረጋገጡ ድረስ የረ ኣምባገነናዊ ስርኣቱን ትግል ኣጠናክሮ ከመቀጠል ውጪ ሌላ ኣማራጭ ኣይታይም። ስለዚህም የኢምፓየሪቷ ህዝቦች በተለይም ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ በጠላት ኣሳሳችና ከንቱ ተስፋ የተሞሉ ፕሮፓጋንዳዎች ሳይታለሉ ለነጻነታቸው የሚያካሄዱትን ትግል ኣጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ በማናቸውም ኣጋጣሚዎች ሊከሰቱ የሚችሉትን እድሎች ለትግላቸው ስኬታማነት ለማዋል ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ኦነግ ጥሪ ያቀርባል።

ዛሬ የህዝቦች ንቃተ ህሊና ደረጃ እየጎለበተ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በጠላት ጎራ ውስጥ እየታየ ያለው ክስተት ለነፃነት ትግላችን የተሻለ እድል በመፍጠር ላይ ይገኛል። ባሁኑ ወቅት በሃገር ቤት የሚታየው የትግላችን ሁኔታ ኣበረታች መልክ ያለው ቢሆንም በፖለቲካ ድርጅቶችና በመሰል ሃይሎች መካከል የሚስተዋለው እውነታ ግን ኣሳሳቢ መሆኑ የሚታበል ኣይደለም። ድክመቶቻችንን በማረም ኣሁን በተከሰተው የታሪክ ኣጋጣሚ ተጠቅመን ፍትሃዊ ትግላችንን ከግቡ ማድረስ ይጠበቅብናል። በመሆኑም የድርጅቶችና የኣንጃዎችን ቁጥር እያበራከትን በተናጠል መታገል ምንም ኣይነት ድል እንደማያስገኝ በመገንዘብ በኦሮምያ ሉኣላዊነትና በኦሮሞ ህዝብ ነፃነት የሚያምኑ ድርጅቶች ወደ ኣንድነት በመምጣት የነፃነት ትግሉን ጎራ እንዲያጠናክሩ ኦነግ ጥሪውን ያድሳል። ይህንን ለማሳካትም ከበኩሉ የሚጠበቀውን ድርሻ በብቃት ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን ያስገነዝባል። በሃገር ቤትና በውጪው ኣለም የሚገኘው ህዝባችንም ይህንን ተገንዝቦ የታጋዮቻችንን ኣንድነት በማጎልበት ረገድ የሚጠበቅበትን የዜግነት ድርሻውን እንዲያበረክት ኦነግ ጥሪውን ያቀርባል።

በሃገር ቤት ህዝባችን የሚገኝበት ሁኔታ በእጅጉ የከፋ መሆኑ ሃቅ ነው። ከመሬቱ መፈናቀል፣ ስራ ኣጥነት ከመበራከቱ የተነሳ የኑሮው ሁኔታ መቃወስና የኑሮ ውድነትን መቋዋቋዋም ኣቅቶት ለልመና ህይወት መዳረግ ህዝባችንን ከገጠሙት ኣሳሳቢ ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። ከኣምባገነናዊው መንግስት ግድየለሽነት የተነሳ የተፈጥሮ ኣካባቢ ከፋብሪካዎች በሚለቀቅ መርዛማ ፈሳሽ ተበክሎ ሰብኣዊና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ሲከስት በገሃድ እየታየ ነው። ከዚህም

በተጨማሪ ስርኣቱ ለህዝባችን ካለው ጠላታዊ ስሜት የተነሳ ህዝባችንን የእስራቱና የግድያው ዋና ኢላማ ማድረጉ ባሰበት እንጂ ኣልተሻሻለም። ስለዚህም ህዝባችን የሚያዋጣው የተያያዘውን የመብት ትግል ማፋፋም ብቻ መሆኑን ተገንዝቦ እጅግ ኣስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ የጀመረውን የኣልገዛም ባይነት ኣመጽ ኣጠናክሮ እንዲቀጥል ኦነግ ጥሪውን እያደሰ ይህንን ህዝባዊ ትግል ለማሳካትም ከህዝቡ ጋር በቁርጠኝነት መቆሙን ያረጋግጣል።

የወያኔ መንግስት ህዝቦችን ማጋጨት፣ ኣንድን ህዝብ ሳይቀር ከፋፍሎት ማባላትን ጨምሮ በሃይማኖት ጉዳዮች ውስጥ እጁን በማስገባት በምእመናን መካከል መቃቃር እንዲፈጠር ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ኦነግ ይህንን የወያኔ መንግስት እኩይ ተግባር እያወገዘ በተለይም ደግሞ ሙስሊሙ ማህበረሰብ የጀመረውን የሃይማኖት ነፃነት ጥያቄ ኣጠናክሮ እንዲቀጥል መልእክታችንን እናስተላልፋለን።

በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተወላጆች ከወያኔ መንግስት ወከባና የጭካኔ እርምጃ በመሸሽ ዛሬም ወደ ጎሮቤት ሃገራት እየተሰደዱ ናቸው። ይሁን እንጂ በተሰደዱባቸው የጎሮቤት ሃገራትም ቢሆን የሚደርስባቸው ሰቆቃ በእጅጉ ዘግናኝ ነው። በኦሮሞ ስደተኞች ላይ በሚፈመው በደል ውስጥ የኣንዳንዶቹ ሃገራት እጅም ይገኝበታል። ስለሆነም ከኦሮሞ ህዝብ ጋር የሚጎራበቱ የየሃገራቱ መንግስታትና ህዝቦች መንግስታት ሃላፊ ህዝቦች ግን ህያው መሆናቸውን ኣውቀው በታሪክ ላይ ለተመሰረተው ህዝባዊ ወዳጅነት ቅድሚያ በመስጠት የኦሮሞ ስደተኞችን የስደተኝነት መብት ኣንዲንከባከቡ ኦነግ ይጠይቃል። በተለይም መንግስት ነኝ የሚለው የሶማሊ ላንድ ኣስተዳደር በUNHCR ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸውን ጨምሮ በሃገሪቷ የሚገኙትን የኦሮሞ ስደተኞች በሃይል ወደ መጡበት መመለስ፣ ማሰር፣ ማዋከብ፣ መግደልና ህጻናት ሳይቀሩ በእሳት እየፈጁ መግደልን የመሳሰሉ የጭካኔ ተግባራቱን ባስቸኩዋይ እንዲገታ ኦነግ በኣፅንኦት ያሳስባል።

የኦነግ ህዋሶችን ጨምሮ በሃገር ቤት የሚካሄደው ህዝባዊ ትግልና መነሳሳት በመላው ኦሮምያ ከምን ጊዜውም በላይ የሚስተዋል መሆኑ የህዝባችን ፍላጎትና ኣላማ ምን እንደሆነ ያስገነዝባል። ይህ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ታምኖ በተለይም ቄሮው (ወጣቱ ትውልድ) የተያያዘው የረ ጭቆና ኣመፅ በህዝባችን ዘንድ ሰፊና ያልተቆጠበ ድጋፍ እንዲያገኝ ኦነግ ጥሪ ያቀርባል።

ለተጨቆኑ ህዝቦች መብት መረጋገጥ የሚታገሉ ሃይሎች ሁሉ በትግሉ ሂደት ውስጥ መደጋገፍና መተባበር እንዳለባቸው የወቅቱ ኣንገብጋቢ ጥያቄ ነው። ኦነግ ህዝባቸውን ከጭቆና ለማላቀቅና ለህዝባቸው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት መረጋገጥ ከሚታገሉ ሃይሎች ጋራ የትግል ኣጋርነቱን ለማጠናከር ከማናቸውም ጊዜ በላቀ መልኩ የሚሰራ መሆኑን እያስገነዘበ ህዝባችንም ይህንን ኣላማ ለማሳካት የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት ጥሪ ያስተላልፋል።

የኢትዮጵያን ኢምፓየርነት እንዳለ ለማቆየት ሲሉ የህዝቦችን መብት ኣውቀው መቀበል ተስኖኣቸው ኣሮጌውን ስርኣት ለመመለስ የሚያልሙ ሃይሎች የተከተሉት ጎዳና የማያዋጣና ህዝቦችን ለርስ በርስ ግጭት የሚጋብዝ መሆኑን ተገንዝበው ከዚያ ይልቅ እውነተኛ ዴሞክራሲ፣ ነፃነትና እኩልነት ይሰፍን ዘንድ በቅንነት እንዲታገሉ ኦነግ

ይጠይቃል።

የወያኔ መንግስት እንደ ኣሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ የኣውሮፓ ህብረትና ቻይና ያሉት ሃያላን መንግስታት በሚያደርጉለት የወታደራዊ፣ የኢኮኖሚና የድፕሎማሲ እርዳታ በመታገዝ ኢትዮጵያን እስከ ዛሬ ድረስ መግዛት ችሏል። ከነዚህ ሃይሎች በሚያገኛቸው እርዳታዎችም እየታገዘ ይበልጥ የሰብኣዊ መብቶችን ይረግጣል። ስለሆነም እነዚህ ሃያላን መንግስታት ለሰብኣዊ መብቶች ረገጣ መባባስ እየዋለ ያለውን እርዳታቸውን ለወያኔ መንግስት መስጠት እንዲያቆሙ ኦነግ በኣፅንኦት ይጠይቃል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

መስከረም 9, 2012